# ልዑል እግዚአብሔር፡

# እንኳን፡ ለ፳፻፲፫ (፪ሺ፲፫)ኛው
# የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት እና
# የቃና ዘገሊላ ከብካብ፥ እንዲሁም፡
# ለቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ሥጋና
# ለኪዳነ ምሕረት በዓላት፡ በደኅና አደረሰን!

---

በታኅሣሥ ፩ ቀን ከሚውለው፡ ከበዓለ ትስብእት እኩለ ሌሊት በኋላ፡ በታኅሣሥ ፪ ቀን አጥቢያ የሚጀምረው፡ ጾመ ማርያም፡ "ከተራ" በሚባለው፡ ጥር ፲ ቀን በሚውለው፡ የጥምቀት ዋዜማ ያበቃል፡፡

በማግሥቱም፡ ጥር ፲፩ ቀን የሚውለው፡ **ታላቁ፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የጌታችንና የመድኃኒታችን፥ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ጥምቀት፡** የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰተ ሥጋዋ በዓል እስከሚከበርበት፡ እስከጥር ፳፩ ቀን ድረስ፡ በከፍተኛ የሐሤት መንፈስ፥ የረቡዕና የዓርብ ጾምም በሌለበት፡ የፋሲካ ደረጃ ይከበራል፡፡

ከዚህ፡ ከጌታችን በዓለ ጥምቀት ተነሥቶ፡ ጥር ፳፩ ቀን በሚውለው፡ በእናታችንና ንግሥታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፍልሰተ ሥጋዋ በዓል በኩል አልፎ፡ የኪዳነ ምሕረት ዓመታዊ በዓለ ዝክር እስከሚውልበት፡ እስከየካቲት ፲፮ ቀን ድረስ ባሉት ወራትና ሳምንታት ውስጥ ስለሚከበሩት በዓላት፡ የሚከተለውን ማብራሪያ አቅርበንላችኋል፡-

## ዘመነ አስተርእዮ፡፡

"አስተርእዮ" ምን ማለት ነው? ለምሳሌ፡ "አስተርእዮ ማርያም" እየተባለ፡ በዘልማድ እንደሚነገረው አባባል፡ በበዓላት ላይ እየተቀጸለ የሚደመጥ ዘይቤ አለ፤ ግን፡ እንዲህ የሚባለው፡ ለምን እንደኾነ፡ ልናውቀው ይገባል፡፡

“አስተርእዮ”፡ “ታየ”፤ “ተገለጠ” የሚል ትርጕም ካለው፡ “ተርእየ” ከሚለው የግእዝ ቃል፡ የተገኘ ነው፤ “በገሃድ መታየት”፥ “በይፋ መገለጥ” ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ከበዓለ ጥምቀት አንሥቶ፡ **እስከበዓለ-ኢትዮጵያ** (እስከጾመ ኢትዮጵያ = ጾመ ነነዌ) ድረስ ያለው ጊዜ፡ “ዘመነ አስተርእዮ” ይባላል። እንዲህ የተባለበትንም ምክንያት፡ ከዚህ የሚከተለው ሐተታ ያብራራዋል፦

**አስተርእዮ፡** “'የዲያብሎስን የክፋት አገዛዝ፥ የኃጢአትን ጽኑ ቀንበርና የሞትን የማይቀር ፍዳ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ በመደምሰስ፡ ፍጥረቱን ኹሉ ለማዳን፡ ወደዓለም ይመጣል!' ተብሎ፡ ትንቢት ተነግሮለትና ሱባኤ ተቆጥሮለት፡ በተስፋ የሚጠበቀው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ፍጹም ሰው በመኾን፡ እግዚአብሔር እም፡ አስቀድማ በተዋሐደቻት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ያለወንድ ዘር ተፀነሰ፤ ከእርሷ፡ በድንግልና ተወልዶ፡ "ወልደ-ዕጓለ-እመሕያው" = "የማርያም ልጅ” ተባለ፤ ከኃጢአት በቀር፡ በኀውን፡ የሰውን ሥራ እየሠራም፡ ለሠላሳ ዘመን በምድር ላይ ተመላለሰ። ከዚህ በኋላ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ቆሞ ሳለ፡ አባቱ፡ እግዚአብሔር አብ፡ ድምፁን በማሰማት፥ መንፈስ ቅዱስ፡ በርግብ አምሳል፡ ራሱ ላይ በመቀመጥ፥ እርሱ ራሱም፡ በአዋጅ ነጋሪው፡ በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ፡ ማንነቱን፡ በይፋ ገለጠ።

ይህ ወራት፡ የማይታየው፡ የአምላክ አካልና ባሕርይ፡ ከሚታየው፡ የሰው አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ የተገለጠበት ማንነቱ፡ በገሃድ የታወቀበትን ምሥጢር በማብራራት፡ ምሥራቹ የሚነገርበት፥ በዚህ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊትም፡ ሰው ኹሉ፡ ደስታውን የሚፈጽምበትና ምስጋናውን፡ ለፈጣሪው የሚያቀርብበት ጊዜ ስለኾነ፡ “ዘመነ አስተርእዮ” መባሉ፡ ትክክልና ተገቢ ኾኖ ይገኛል።

ከጥምቀት ጋር፥ ከእርሱም በኋላ፡ በዚሁ፡ በዘመነ አስተርእዮ የሚከበሩት በዓላት፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

## በዓለ ጥምቀት።

ጥምቀት፡ በክርስቲያኑ ዓለም ካሉ ሕዝቦች ኹሉ ተለይቶ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ብቻ፡ በታላቅ ድምቀት ይከበራል። የዚህንም ምክንያት ማወቁ፡ ለእየራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎችም ለማስረዳት ይጠቅማል፤ ያስፈልጋልም።

ምክንያቱ፡ እንዲህ ነው፡- በዘመነ አስተርእዮ ከሚከበሩት በዓላት መካከል፡ ዋናው፡ እንደምታውቁት፡ “ጥምቀት” ነው፡፡ በተዋሕዶ የከበረው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት፡ ለዓለሙ ተገልጦ የተመሰከረበት፥ መታሰቢያውም፡ ጥር ፲፩ ቀን እንዲውል የተደረገው፡ የጥምቀቱ በዓል፡ “ከተራ” ከሚባለው፡ ከዋዜማው ጀምሮ፡ በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡

ለበዓሉ ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን፡ ባሕረ ጥምቀት፡ ውኃውን፡ ከወንዝ፡ በቦይ መርተውና ከትረው (ገድበው) የሚያዘጋጁበት፥ ለመንበረ ታቦቱ ማሳረፊያና ለቀዳስያኑ ማገልገያ፥ ለደባትሩም ማሕሌት መቆሚያና ለምእመናኑ መሰባሰቢያ የሚኾኑት ድንኳኖች የሚተከሉበት፥ በዚያ፡ በባሕረ ጥምቀቱ አካባቢ የሚያድረውም ሰው፡ በየወገኑ፡ የየራሱን ዳስ የሚቀልስበት ዕለት ስለኾነ፡ ይህ፡ የጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ “ከተራ” ይባላል፡፡ “መከተር” (ውኃ መገደብ) ከሚለው ቃል የወጣ ነው፡፡

በዘመነ ኦሪት፡ እሥራኤል፡ ከግብፅ ከወጡ በኋላ፡ “ምድረ ርስት” ወደተባለችው፡ የከነዓን አገር ከመግባታቸው በፊት፡ አርባ ዓመት ሙሉ፡ በሲና ምድረ በዳ ሲንከራተቱ፡ ማደሪያቸው፡ ድንኳንና ዳስ ስለነበረ፡ የኋላ ትውልድ፡ ያን፡ የመከራና የፈተና ዘመን እንዳይረሳ፡ “የዳስ በዓል” እያሉ፡ በያመቱ እንዲያከብሩት፡ እግዚአብሔር አዝዟቸው ነበረ፡፡

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኪዳነ ኦሪቱ የብሉዩ ዘመን፡ በዚያው፡ በኦሪቱ ሥርዓት፡ ስናከብረው ከቆየን በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በዘመነ ክርስትና፡ በጥምቀት ተክተን፡ በዓሉን፡ እነሆ፡ ዛሬ በሚታሰብበት መልክ፡ ማክበራችንን ቀጠልን፡፡ ስለዚህ፡ ካህናቱ፡ በተንቈጠቈጠ መጎናጸፊያ ተሽክመው፡ በዝግታ እየተራመዱ፡ በክብር የሚያኳኍዙት፡ የአዲስ ኪዳኑ ታቦት፡ በተለያዩ ቀለማት ባሸበረቁ፡ የተዋቡ አልባሳተ ተክህኖ በተሸለሙ፥ መብራትና መስቀል፥ የማዕጠንተ ወርቅ ጽንሓ፥ ዣንጥላና ድባብ በያዙ ልኡካን ተከብቦ፥ በማኅሌታውያኑ ደባትር ሃሌታ፥ በወጣት መዘምራን ዜማና ደስታ፥ በወንዶች ሆታና በሴቶች እልልታ ታጅቦ፡ በበዓሉ ዋዜማ፡ ከቤተ መቅደሱ ይነሣል፡፡

በዚህ መልክ፡ ወደወንዝ፥ ወይም፡ ወደከተራው ቦታ ይወርድና በዚያው አድሮ፡ በማግሥቱ፡ በዋናው የጥምቀት በዓል ዕለት፡ በታላቅ ብሔራዊ ክብር፡ ወደመካነ መንበሩ ይመለሳል፡፡ ለዚህ ሥርዓታችን መነሻ የኾነውን ምክንያት፡ እንዲህ በሚል ቃል እናጠቃልልላችኋለን፡-

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በጥምቀት በዓል የምናካኺደው ሥርዓት፡ እግዚአብሔር፡ ለእሥራኤል ልጆች፡ “አወርሳችኋለሁ!” ብሎ፡ ተስፋ ወደሰጣቸው ምድረ ርስት ይገቡ ዘንድ፡ የኢየሱስ መሲሕና የድንግል ማርያም ቀዳሚት አርአያ የኾነችውን ታቦተ ጽዮንን፡ የኦሪቱ ካህናት ተሸክመው፡ የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲያቋርጡ፡ ትእዛዝ ሰጧቸው፡ ወንዙን ሲሻገሩ፡ የወንዙ ውኃ፡ ከኹለት ተከፍሎና በራሱ ኃይል ተከትሮ፡ ቆሞላቸው፡ ሕዝቡ፡ በቀይ ባሕር በኾነው ዓይነት፡ በደረቁ መሬት ለመሻገር የቻሉበትን የእግዚአብሔርን ቸርነት ያስታውሰናል፡፡

እንደዚያን ጊዜ ኹሉ፡ ዛሬ፡ በዘመነ ሓዲስ ደግሞ፡ አማናዊቷ÷ ሕያውቷና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው፡ አማናዊው÷ ሕያዊውና ዘለዓለማዊው ጽላተ ኪዳን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ፡ በዮሓንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ፡ በእርሱ ጥምቀት፡ እኛ፡ ከዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ ወጥተን፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር እንድንቀዳጅ ማድረጉን እንዳንዘነጋ÷ ከዚህ የተነሣም፡ ከኃጢኣት፡ ወደጽድቅ [ከሓሰት፡ ወደእውነት]÷ ከሞት፡ ወደሕይወት ተሻግረን፡ ዘለዓለማዊቷን የእግዚአብሔርን መንግሥት የወረስን መኾናችንን ያረጋግጥልናል፡፡

የቤተ ምልክናው ሠራዊት፡ “ተመልከት ዓላማህን! ተከተል አለቃህን!” በሚለው መርኆው መሠረት፡ ከታቦቱ ፊት፡ “**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር! = ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!**” እና “**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ! = ከይሁዳ ነገድ የተወለደው አንበሳ፡ ድል አደረገ!**” የሚለው መለኮታዊ ማኅተም በመኻሉ የሠፈረበትን፡ የባለመስቀል መፆር ሰንደቅ ዓላማውን አንግቦ ይቀድማል፤

-በመካከሉ፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ የኾኑት መዘምራኑ ቀጥለው፡ በመቋሚያና በጸናጽል÷ በከበሮና በማኅሌት እያሸበሸቡ ይጓዛሉ፡፡ ከታቦቱም በኋላ፡ የቤተ ክህነቱ÷ የቤተ ምልክናውና የቤተ ሕዝቡ ባለሥልጣኖች፡ ታቦቱን ያጅባሉ፡፡

-ከዚያም፡ በመጨረሻ፡ የቤተ ሕዝቡ ወገን የኾነው፡ ወንዱም፡ ሴቱም÷ ሕፃኑም፡ ሽማግሌውም፡ ፀዓዳ (ነጫጭ) የክት ልብሱን ለብሶ፡ በሆታና በእልልታ ይከተላል፤

ይህም የሚኾነው፡ ከኪዳነ ልቦናው ዘመን ጀምሮ፡ ሲሠራበት ከቆየው፡ ከጥንታዊው የኢትዮጵያ ልጆች ሥርዓት ጋር ተዋሕዶ የቀጠለውን፡ የመካከለኛውን፡ የኪዳነ ኦሪቱንና የመጨረሻውን፡ የኪዳነ-ምሕረቱን ዘመናት ሥርዓት ለማስታወስ ያህል ነው::

ያም፡ እሥራኤላዊው ንጉሥ ዳዊት፡ ታቦተ ጽዮን፡ በእሥራኤል ካህናትና ሕዝብ ተረስታና ተጥላ ከነበረችበት ሥፍራ፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ፡ በዐጀብ አምጥቶ፡ ባዘጋጀላት የማረፊያዋ ድንኳን ውስጥ ባስገባት ጊዜ፡ ከከብት እረኝነት አንሥቶ፡ ለሕዝብ መሪነት ባበቃው ፈጣሪው ፊት፡ ከደስታው ብዛት የተነሣ፡ ራሱ፡ በካህናቱና በሕዝቡ ፊት ዐብሮ እየዘመረ፥ እያጨበጨበና እያሸበሸበ፡ የምስጋና ስሜቱን የገለጸበትን ባህል የመሰለው መኾኑ ነው::

## ጥምቀት፡ የእኛም፡ የየግላችን በዓል ስለመኾኑ::

የጥምቀት በዓል፡ የኢየሱስ መሲሕ በዓል ብቻ አይደለም፤ የእኛ፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያትም በዓል ብቻ አይደለም። ያመንነው እኛም፥ በእምነት የጠፋት አይሁድም፥ ያላመኑት አሕዛብም፡ በእርሱ ጥምቀት ተቀድሰንና ተጠምቀን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን የበቃነው፡ የኹላችንም፡ የሰው ልጆች በዓል ጭምር ነው እንጂ::

በዓሉ፡- -በመጀመሪያ ነገር፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በአዲሱ ኪዳን፡ የራሱን ማንነት፡ ለዓለም የገለጸባትንና ያስመሰከረባትን፡ ጥምቀቱንና ቀኒቱን ያስታውሰናል፤

-ቀጥሎ፡ የኹሉ ፈጣሪና አምላክ የኾነው እርሱ የተጠመቀው፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ በማሕፀን ከተጠመቅንባት ቅጽበት ጀምሮ፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ለኾንነው፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያትም ሳይኾን፡ ከኢትዮጵያዋ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ ተወልዶ፡ "የጠፉትን፡ የእሥራኤልን ቤት በጎች" ያዳነበትን፥ ለእነርሱም፡ አብነት ያደረገውን፡ የጥምቀትን ሥርዓት፡ ራሱ ፈጽሞ፡ እነርሱም፡ ያንኑ ሥርዓት በመፈጸም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለው፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን እንዲበቁ ያደረገበትን፡ አምላካዊ ፍቅርና ቸርነት፥ ከዚህ የተነሣም፡ ኹላችንም የተቀዳጀነውን፡ ይህን፡ ወደር የሌለውን ዘለዓለማዊ የመጨረሻ ክብር፡ አጉልቶ ያሳየናል:: (ማቴ. ፲፥ ፭-፯፤ ፲፭፥ ፳፬።)

አዎን! ሓዋርያው፡ "ወርእዩ፡ ዘከመ እፎ ፍቅሩ፡ ዘወሀበነ አብ፡ ከመ ውሉደ እግዚአብሔር ንኩን! ወኮነሂ።" ማለትም፡ “'የእግዚአብሔር ልጆች' ተብለን ልንጠራ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ! እንዲሁም ነን፡፡” ያለውን በማዘከር፡ የጥምቀትን በዓል፡ እኛ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወልደንና ለዘለዓለም ሕይወት ተጠርተን፡ “'የእግዚአብሔር ልጆች' የተባልንበትና የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች፥ አገልጋዮቹ ካህናትም የኾንንበት፡ የየራሳችን የልደት በዓል ነው!” ብለን፡ አምነን፡ በንጹሕ ምስጋናና በፍጹም ደስታ፡ የምናከብረው ታላቅ በዓላችን ነው፡፡ (፩ኛ ዮሐ. ፫፥ ፩፡፡)

እዚህ ላይ፡ አንድ፡ ሊታወቅ የሚገባው የእግዚአብሔር እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ እውነተኞቹ "የእሥራኤል ልጆች"፡ እኛ፡ የቀድሞዎቹ፥ የዛሬዎቹም የኢትዮጵያ ልጆች መኾናችንን፡ በትክክል የመገንዘቡ ቍም-ነገር ነው። የዚህም፡ ምክንያት፡ እንዲህ ነው፡-

፩ኛ፡ እየራሳቸውን፡ "እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች ነን!" እያሉ፡ የሚመጻደቁት "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" የተባሉት የብሉይ ዘመኑ ኦሪታውያን ወገኖች፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው መፈጸም ስላቃታቸው፡ እኒሁ፡ ሦስቱም ቃል-ኪዳናት፡ ወደኢትዮጵያ ልጆች፡ በአደራነት ተመልሰው፡ እነሆ፡ በእነርሱ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ለዝንተ-ዓለም፥ እስከዛሬና ለዘለዓለም፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን አግኝተው የኖሩ፥ እየኖሩም ያሉ በመኾናቸው ነው።

እንዲሁም፡ ከእነዚያ፡ ከቀደሙት፡ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ከተባሉት፡ የብሉይ ዘመኑ ኦሪታውያን ወገኖች መካከል፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በየዘመናቱና በየምክንያቱ፡ ከእነዚሁ ቃል-ኪዳናት ጋር፡ ዐብረው የመጡት፥ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ እንዲሁም፡ በቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ በተገኘው የሥጋ ልደት፡ ከቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጋር የተዋሓዱት፡ "እውነተኞቹ የእሥራኤል ልጆች" በመኖራቸው ጭምር ነው።

፪ኛ፡ ነገር ግን፡ እየራሳቸውን፡ "እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች ነን!" እያሉ፡ የሚመጻደቁት፥ ደግሞም፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው መፈጸም ያቃታቸው፡ እነዚያ፡ የጥንቶቹ ኾኑ፡ የዛሬዎቹ፡ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" የተባሉት፡ አሪታውያን ወገኖች፡ ቀድሞም፡ በሙሴ ጊዜ፥ በመጨረሻም፡ በኢየሱስ መሲሕ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች፥ ከሃዲዎችና ገዳዮች ኾነው በመገኘታቸው፡ "እሥራኤል"፥ ወይም፡ "የእሥራኤል ልጆች" ሊባሉ የማይቻል መኾኑን በማረጋገጥ፡ በመለኮታዊው ቃል፡ ምን እንደተባሉ ታውቁ የለምን? በዚህ ረገድ የተመዘገበውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የአዲስ ኪዳን መጽሐፋዊ ጥቅስ ተመልከቱት፡-

ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች፥ ከሃዲዎችና ገዳዮች ኾነው ለተገኙት፡ ለእነዚያ ለቀድሞዎቹና ለእነዚህ፡ ለዛሬዎቹ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ለተባሉት፡ የአሪታውያን ተከራካሪዎቹ ወገኖች፡ የተናገረው ቃል፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "'ወአንሰ፡ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ፡ እነግር። ወአንትሙኒ፡ ዘርኢክሙ በኀበ አቡክሙ፡ ትገብሩ።'

"ወአውሥኡ፥ ወይቤልዎ፡- 'ለነሰ፡ አብርሃም አቡነ።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ ውሉደ-አብርሃም አንትሙ፡ ግብረ አብርሃም፡ እምገበርክሙ። ወይእዜሰ፡ ተኀሥሡ ትቅትሉኒ፥ ብእሴ ጻድቀ፤ ዘጽድቀ እነግረክሙ፤ ዘሰማዕኩ በኀበ እግዚአብሔር፤ ወአብርሃምሰ፡ ኢገብረ ከመዝ። አንትሙሰ፡ ትገብሩ፡ ግብረ አቡክሙ።'

"ወይቤልዎ፡- 'ንሕነሰ፡ ኢተወለድነ እምዝሙት፤ አላ አሐዱ አብ ብነ፤ ወውእቱ እግዚአብሔር።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ እግዚአብሔር አቡክሙ፡ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ፤ ወቃልየኒ፡ እምዐቀብክሙ፤ እስመ አነ፡ እምኀበ እግዚአብሔር ወጻእኩ፤ ወመጻእኩ፤ ወአኮ ለልየ ዘመጻእኩ፤ አላ ውእቱ ፈነወኒ። እፎ እንከ፡ ኢተአምኑ ቃልየ? እስመ ኢትክሉ ሰሚዐ፡ ነገረ ዚአየ።

"'<u>አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፤ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ።</u> ወውእቱሰ ቀታሌ ነፍስ ሰብእ ውእቱ እምትካት፤ ወኢይቀውም በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ፤ ወሶበሂ ይነብብ ሓሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሓሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሓሰት።

"'ወአንሰ፡ እስመ ጽድቀ እነግር፡ ወኢተአምኑኒ። መኑ እምኔክሙ፡ ዘይዛለፈኒ በእንተ ኃጢአት? ወእመሰ፡ አነ ጽድቀ እነግር፡ ለምንት ኢተአምኑኒ። <u>ዘሰ እምእግዚአብሔር ውእቱ፡ ቃለ እግዚአብሔር ይሰምዕ፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አንትሙሰ፡ ኢትሰምዑኒ፤ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር።"</u>

ማለትም፡ "'እኔ፡ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን አናገራለሁ። እናንተም ደግሞ፡ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።'

"መልሰውም፡- 'አባታችንስ፡ አብርሃም ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም፡- 'የአብርሃም ልጆች ብትኾኑማ፡ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። አኹን ግን፥ ከእግዚአብሔርም ዘንድ የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን፡ የእውነት ሰው እኔን፡ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። አብርሃም፡ እንዲህ አላደረገም። እናንተ ግን፡ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ፤' አላቸው።

"እነርሱም፡- 'እኛስ፡ ከዝሙት አልተወለድንም፤ ነገር ግን፡ አንድ አባት አለን፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም አላቸው፡- "እግዚአብሔር፡ አባታችሁ ቢኾንማ ኖሮ፡ እኔን፡ በወደዳችሁኝ፥ ቃሌንም፡ በጠበቃችሁ ነበር፤ እኔ፡ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ፡ ላከኝ እንጂ፡ ከራሴ የመጣሁ አይደለሁም። እንኪያ፡ ቃሌን እንዴ ታምናላችሁ? የምነግራችሁን፡ መስማት አትችሉምና።

<u>"እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአባታችሁን ፈቃድ ልትፈጽሙ ትወድዳላችሁ።</u> እርሱም፡ ከጥንት፡ የሰው ነፍስ፡ ገዳይ ነው፤ እውነት በእርሱ ዘንድ ስለሌለች፡ ለእውነት አይቆምም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራልና፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰት አባትም ነውና።

"እኔንማ፡ እውነትን ስለምናገር፡ አታምኑኝም። ከእናንተ፡ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ፡ ማነው? እኔ ግን፡ እውነትን የምናገር ከኾንሁ፡ ለምን አታምኑኝም? ከእግዚአብሔር የኾነ፡ እርሱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ ስለዚህም፡ እናንተ አትሰሙኝም፤ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና።'" (ዮሓ. ፰፥ ፵፮-፵፯።)

አዎን! በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው፡ "እውነተኞቹ እሥራኤል፥ የእሥራኤልም ልጆች፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የኾንነው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ነን እንጂ፡ ዛሬ፡ ራሳቸውን፡ 'እሥራኤል ነን!' የሚሉት፡ አይሁድ አይደሉም!" ያሰኘውና የሚያሰኘው።

## የጥምቀትን በዓል፡
## እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፡ እንዴት እንደምናከብር?

በዓለ ጥምቀትን፡ እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፡ ከሌላው የክርስቲያኑ ዓለም ሳይቀር፡ ተለይተን፡ እጅግ በተመሰጠ፡ መንፈሳዊ ስሜት የምናከብርበትን ምክንያት የሚያመለክተውን፡ እንዲህ የሚለውን አጭር ትንተና፡ በማጠቃለል አቅርበንላችኋልና፡ ይህን ደግሞ፡ ተመልከቱት፡-

፩ኛ፡ "በኖኅ ዘመን፡ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት፡ ደጅ እየጠኑ የነበሩት፡ ጥቂቶቹ፡ ስምንት ሰዎች፡ መርከብ ሠርተው፡ ከጥፋት ውኃ እንደዳኑባት ኹሉ፡ አኹንም፡ እኛን፡ በዚያው አምሳል፡ በጥምቀት ያድነናል፤ ሥጋን፡ በእድፍ በመታጠብ አይደለም፤ በእግዚአብሔርና በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በማመናችን፡ በበጎ ሕሊና የሚፈጸመውን መልካም ግብር ያስተምረን ዘንድ ነው እንጂ።" በሚለው የመጽሓፍ ቃል መሠረት፡ እግዚአብሔር፡ የኪዳኑ ልቦናዋን የኖኅ መርከብ፡ በባሕረ ነጋሽ (በኤርትራ) ላይ ያሻገረበት፡ መለኮታዊና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ተጠብቆ ሲሠራበት የቆየ በመኾኑ ነው፤ (፩ጴጥ. ፫፥ ፳-፳፩።)

፪ኛ፡ ኢያሱ፡ የኪዳኑ ኦሪቷን፡ የእግዚአብሔር ታቦት በተሸከሙ ካህናት፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ በዮርዳኖስ ባሕር የማሻገሩ ዜና መዋዕል ዐብሮ የሚገኝበትን፡ ቀደም ብለን ያወሳንላችሁን፡ የታቦተ ጽዮንን ዝክረ ነገር የሚያካትተው፡ የኪዳኑ ኦሪቱ ሥርዓት፡ በኢትዮጵያ፡ ከቀደመው ጋር ተዋሕዶ፡ እንዲቀጥል በመደረጉ ነው፤ (ኢያ. ፫፥ ፩-፲፯።)

፫ኛ፡ ትንቢቱ ኹሉ ተፈጽሞ፥ ተስፋውም ኹሉ ደርሶ፡ እግዚአብሔር፡ ሰው መኾኑ ከተገለጸ በኋላ፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ይካኼድ የነበረው፡ የንስሓ ጥምቀት ሳይቀር፡ ጌታችን፡ ለኒቆዲሞስ በገለጸው የጥምቀት ምሥጢር መሠረት፡ የኪዳነ ልቦናውና የኪዳነ አሪቱ ሥርዓታት፡ ኹሉም፡ በአዲሱ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ታድሰው፡ ዛሬ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፡ የአዲስ ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት፡ ወደወንዙ፥ ወይም፡ ወደከተራው የሚወርዱበት ሥርዓት በመተካቱ ነው:: (ዮሐ. ፫፥ ፩-፲፩::)

እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚህ በዓላችን ጊዜ፡ **"ክርስቶስ ተጠምቀ እሰይ! ወለደነ ዳግመ እማይ!"** ማለትም፡ "ክርስቶስ፡ ስለተጠመቀ ደስ ይበለን! እኛም፡ በጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ፡ እንደገና እንድንወለድ አደረገ!" ከሚለው ዝማሬያችን ጋር፡ **"ዮም ፍሥሓ ኮነ! በእንተ ጥምቀቱ ለክርስቶስ!"** የሚለውን የምሥራች ቃል፡ እንለዋወጣለን:: ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እንደዘመነ ትንሣኤ፡ እስከጥር ፳፩ ቀን ድረስ ይቀጥላል::

በበዓሉ ዕለት፥ ከዚያም ጀምሮ፡ በዚሁ ወራት የሚነገረውናየሚሰማው፥ የሚሰበከውና የሚዘመረው፡ ስለምሥጢረ ጥምቀት ይኾናል::

## ቃና ዘገሊላ::

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በዐዋጅ ነጋሪው ዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ወልድ ማንነት፡ በይፋ ተገልጦ ከታወቀ ወዲህ፡ ወዲያው ተከታትሎ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ይኸው የቅድስት እናቱ እና የእርሱ መለኮታዊ ማንነት፡ በበለጠ ግዙፍ ማስረጃ የተረጋገጠበት የመጀመሪያው ተአምር፡ "ቃና ዘገሊላ" በምትባለው ቦታ፡ ተፈጽሞ ታየ:: ከበዓለ ጥምቀት ቀጥሎና ተያይዞ የሚከበረው "የአስተርእዮ" በዓል፡ "ቃና ዘገሊላ" ይባላል::

"ገሊላ"፡ ዋና ከተማው፡ "ናዝሬት" የኾነ፡ ቀድሞ፡ የፍልስጥኤም፥ ዛሬ፡ የእሥራኤል ክፍለ አገር፥ ወይም፡ አውራጃ ሲኾን፡ "ቃና"፡ በገሊላ የምትገኝ፡ መንደር ናት:: በዓሉ፡ "ቃና ዘገሊላ" የተባለው፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠርተው በተገኙበት ሠርግ ላይ፡ እርሷ፡ በእናትነት፥ ልጇም፡ በልጅነት ደረጃ ተነጋግረው፡ የመጀመሪያው ታላቅ ተአምር የተፈጸመበት ቦታ፡ "ቃና ዘገሊላ" ወይም፡ "የገሊላዋ ቃና" እየተባለ የሚጠራ ስለኾነ ነው::

## ድንግል ማርያም፡
## እግዚአብሔር እም መኾኗና አምላካዊ ቸርነቷ፡
## በይፋ የተገለጸበት ሠርግ።

የቃና ዘገሊላ ዝክረ ነገር፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ይህን ያህል፡ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት፡ በዚህ መልክ የሚከበረው ያለምክንያት አይደለምና፡ ይህንኑ እንግለጽላችሁ!

በዚያ ሠርግ ላይ የኾነውንና የደረሰውን ኹሉ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ እንዲህ ሲል ጽፎታል፡- "በገሊላ ቃና፡ ሠርግ ነበረ፤ የኢየሱስም እናት፡ በዚያ ነበረች፤ ኢየሱስም ደግሞ፥ ደቀ መዛሙርቱም ወደሠርጉ ታደሙ፡፡

"የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ፡ የኢየሱስ እናት፡ 'የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም!' አለችው፡፡

ኢየሱስም፡ 'እናቴ ሆይ! ለምን ታስቸግሪኛለሽ? ጊዜዬ እኮ ገና አልደረሰም!' አላት፡፡

እናቱም፡ ለአገልጋዮቹ፡ 'የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' አለቻቸው፡፡ አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ፡ ስድስት የድንጋይ ጋኖች፡ በዚያ ተቀምጠው ነበር፤ እያንዳንዳቸውም፡ ኹለት፥ ወይም፡ ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር፡፡

"ኢየሱስም፡ 'ጋኖቹን፡ ውኃ ሙሏቸው!' አላቸው፡፡ እስከአፋቸውም ሞሏቸው፡፡ 'አኹን ቀድታችሁ፡ ለአሳዳሪው ስጡት!' አላቸው፡፡ ሰጡትም፡፡

አሳዳሪውም፡ የወይን ጠጅ የኾነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ፡ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን፡ ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪውም፡ ሙሽራውን ጠርቶ፡ 'ሰው ኹሉ አስቀድሞ፡ መልካሙን የወይን ጠጅ፥ ከሰከሩም በኋላ፡ መናኛውን ያቀርባል፤ አንተስ፡ መልካሙን ጠጅ፡ እስካኹን አቆይተሃል፤' አለው፡፡

ኢየሱስ፡ የገሊላ አውራጃ በምትኾን፡ በቃና ያደረጋት፡ የተአምራቱ መጀመሪያ፡ ይህች ናት፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም፡ በእርሱ አመኑ፡፡" (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩፡፡)

ይህ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ የሰው ልጆች ለኾንነው ኹሉ፥ በተለይም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ በቁም ነገር ልናስተውላቸው የሚገቡ መልእክቶችን አስተላልፎልን እናገኘዋለን፡፡ እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ፡ የቅድስት ድንግል ማርያምና የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚያ የሠርግ በዓል ላይ መገኘት፡ “ባልና ሚስት፡ **አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም፤ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን፡ እንግዴህ፡ ሰው አይለየው!**” ብሎ፡ ፈጣሪ አምላክ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን የመሠረተው፥ የኢትዮጵያ ልጆችም፡ በኪዳነ ልቦናና በኪዳነ ኦሪት፡ ጠብቀው ያኖሩት፡ የብሉዩ ኪዳን የጋብቻ ሥርዓት፡ አዲሱ የምሕረት ኪዳን በኾነው፣ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስም፡ መጽናቱንና መጽደቁን፥ መቅቀደሱንም ያረጋግጥልናል። (ዘፍ. ፪፥ ፳-፳፫። ማቴ. ፲፱፥ ፫-፮።)

፪ኛ፡ የሠርጉ በዓል፡ በእርግጥ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ክብር፣ በይፋ የተገለጠበት መኾኑን፡ ራሱ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳል።

በዚያ ቃል መሠረት፡ ያ፡ “ይወርዳል! ይወለዳል!” ተብሎ፡ ትንቢት እየተነገረለትና ሱባኤ እየተቈጠረለት፣ በተስፋ የሚጠበቀው መሢሕ፡ በመካከላቸው የተቀመጠው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፡ የልጇን ማንነትና ክብር፣ ከፅንሰቱ ጀምራ ከምታውቀው፡ ከእናቱ፡ ከድንግል ማርያም በቀር፣ ደቀ መዛሙርቱና የሠርጉ ደጋሾች፥ የእኒህ አገልጋዮችና ሌሎቹ ዕድምተኞች፡ አረጋግጠው አውቀዋል፤ አምነውማል።

ይህም የኾነው፡ ንጹሑን ውኃ፡ በፊታቸው፡ ወደወይን ጠጅነት ለውጦ፡ በተለየ ማለፊያነቱ እያደነቁና እያጣጣሙ እንዲጠጡት ያደረገበትን ተአምሩን፡ በገዛ ዓይናቸው ስለተመለከቱ ነው። ያን፣ ድንቅ ሥራ ያዩት ኹሉ፡ “ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ ነው!” ብለው፡ ከማመን፥ የአምላክነቱንም ክብር፡ አውቀው ከመቀበል በቀር፡ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። ለዚህ እውነታ ምስክርነት፡ “**ኢየሱስ፡ የገሊላ አውራጃ በምትኾን፣ በቃና ያደረጋት፡ የተአምራቱ መጀመሪያ፡ ይህች ናት፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም፡ በእርሱ አመኑ።**” የሚለው፡ የወንጌላዊው መዝገብ ዐረፍተ ነገር የሚበቃ ይኾናል።

፫ኛ፡ እግዚአብሔር፡ ያ፡ መለኮታዊ ድርጊት፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ እንዲፈጸም፥ ያም ተአምር ተጽፎ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ የዓለም ሕዝብና አሕዛብ እንዲያነብቡት ያደረገው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ክብር እንዲገለጽ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ የእናቱ፣ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ማንነትና ክብር፣ በይፋ እንዲታወቅ ለማድረግ መኾኑ፡ ከራሱ፡ ከወንጌላዊው ቃል፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ይኸውም፡ "እናቴ ሆይ! ለምን ታስቸግሪኛለሽ? ፍጥረተ ዓለሙን ለማዳን፡ ሰው የኾንሁት እግዚአብሔር ወልድ፡ እኔ መኾኔን፡ ለዓለሙ የምገልጽበት ጊዜዬ እኮ፡ ገና አልደረሰም!" የሚለው ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ማንነቱን፡ በይፋ የገለጸባቸው፡ ሌሎቹ ብዙዎቹ ታላላቅ ተአምራቱ፡ ገና ወደፊት ተከታትለው የሚፈጸሙ ስለኾነ፡ ይህ፡ የቃና ዘገሊላው የሠርግ በዓል፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን የማስፈለጉ ነገር፡ ይህን ያህል ክብደት የሚሰጠው መስሎ አለመታየቱን፡ የጥቅሱ ኃይለ ቃል፡ በግልጽ ያመለክታል። ይልቅስ፡ የቃና ዘገሊላው የሠርግ አውድማ፡ በመለኮታዊው ዕቅድ የተዘጋጀው፡ ያለጥርጥር፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን ታስቦ መኾኑን፡ ካውድማው የተሰበሰበው የሃይማኖት ፍሬ በሚበቃ ያረጋግጣል።

፩ኛ፡ "ልጄን፡ በሠርግ እድራለሁ!" የሚል፡ ማንም ጨዋ ቤተሰብ፡ የሚደግሠው የድግሥ መጠን፡ ከሚጋብዛቸው ዕድምተኞች (ከሚጠራቸው ተጋባዦች) በላይ የሚትረፈረፍ መኾኑን፥ ያም ባይኾን፡ የሚበቃ መኾኑን፡ በቅድሚያ አውቆና አረጋግጦ የማይዘጋጅ ማነው? ገበታውስ የሚሰናዳው፡ የተጠራው ሰው ብዛት ታውቆ አይደለምን? ይህም ኾኖ፡ ከሙሽራው ጋር የሚመጡት ሠርገኞች ቁጥራቸው እንዲታወቅ ይደረግ የለምን?

ይህ ኹሉ ጥንቃቄ፡ አስቀድሞ የሚደረገው፡ የተደገሠው ድግሥ አንሶ፡ በቤተሰቡ ላይ ኀፍረትና ውርደት እንዳይደርስ ለማድረግ አይደለምን? ድንግል ማርያምና ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሳይኾኑ፡ የልጇ የወዳጇ ደቀ መዛሙርት ጭምር ተጠርተው ከመጋበዛቸው ጋር፡ እመቤታችን፡ "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም!" ብላ፡ የቤተሰቡን ገመና፡ ለልጇ በቀስታ ማዋየቷ፡ ያ ሠርግ፡ የቅርብ ቤተ ዘመዳቸው በዓል መኾኑን፡ አረጋግጦ ያሳያል።

ታዲያ፡ ይህን የመሰለው አሳፋሪ ኹኔታ፡ በዚያ የዘመድ ቤተሰብ ላይ እንዲደርስ፡ በግብዣው ላይ የተሳተፈው መንፈሰ እግዚአብሔር፡ ለምን ፈቀደ? ያ ሠርግ፡ ለመለኮታዊ ዓላማ ማስፈጸሚያ፡ በመለኮታዊ ዕቅድ፡ ኾን ተብሎ የተዘጋጀ መድረክ፡ ወይም አውድማ ቢኾን አይደለምን? ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ በመለኮታዊው ዕቅድ የተዘጋጀው፡ ያ መለኮታዊ ዓላማም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ማንነትና ክብር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ለመግለጽና ለማሳወቅ መኾኑ በዚህ ይታወቃል።

፭ኛ፡ በዚያ የሠርግ በዓል ላይ በተፈጸመው ተአምር ምክን ያት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ታውቆ፡ መለኮታዊ ክብሩ፡ በሰዎች ዘንድ እንደተገለጠ ኹሉ፡ እስከዚያች ቀን ድረስ፡ ሰውና የሰው እናት ብቻ ትመስላቸው የነበረችው፡ ድንግል ማርያም፡ "አምላክን የወለደች" የአምላክ እናት ብቻ ሳትኾን፡ ራሷም፡ እግዚአብሔር እም መኾኗ በይፋ ታውቆ፡ "ወላዲተ አምላክ" የተባለችበት ማንነቷና ክብሩዋ፡ በሰዎች ዘንድ ተረጋግጧል።

፮ኛ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ራሷ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻት፡ "የአምላክ እናት" በኾነችበት፡ በዚህ ማንነቷና ክብሩዋ፡ እንደአምላክ፡ ኹሉን ለማድረግ የሚሣናት፡ አንዳችም ነገር አለመኖሩ፥ ለበጎ ነገር ከኾነም፡ አምላክ፡ ሊያደርግ የማይፈልገውን እንኳ፡ በእናትነቷ፡ ማስደረግ የምትችልበት ሥልጣን የተሰጣት መኾኗ፡ በዚያ ሠርግ ላይ፡ ያለውልውል፡ በይፋ ተመስክሩዋል። ይኸውም፡ "የወይኑ ጠጅ ስላለቀባቸው፡ ሊኾንላቸው የሚገባውን ማድረግ ትችላለህና፡ ልጄ! እኒህን ሰዎች፡ ከዚህ ኀፍረት አውጣቸው!" በሚል መልክ፡ እርሷ ያቀረበችለት ጥያቄ፡ የምስክሩ መነሻ ነው።

እርሱ ደግሞ፡ በቁርጥ ቃል የሰጣት መልስ፡ "እኔ፡ ከአንቺ ሰው ኾኜ የተወለድሁ ብኾንም፡ ኹሉን ማድረግ የምችለው፡ እግዚአብሔር ወልድ እንደመኾኔ፡ በአምላክነቴ፡ የምሠራውን ሥራና፥ ጊዜውንም የምወስን፡ እኔ ነኝ! ስለዚህ፡ ይህን ማንነቴን የምገልጽበትን ተአምር እንዳሳይበት የወሰንሁት ጊዜዬ፡ ገና ስላልደረሰ፡ የጠየቅሽውን ልፈጽምልሽ አልችልምና፡ ተዪኝ!" የሚል መልክ እንደነበረው፡ ከቃሉ፡ ለማስተዋል አያዳግትም።

ይኹን እንጂ፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ይህን የመሰለውን ምላሽ የሰጣት፡ እናቱ፡ ምን ዓይነቱ፡ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳላት፡ ከዚህ የቀጠለው የእናቱ ድርጊት፡ በገሃድ ያሳያል።

እናቲቱ፡ እዚያው፡ በልጇ ዘንድ ቆይታ፡ ሌላ ተጨማሪ ችግሮችን እያከታተለች በማቅረብ፡ ምልጃዋን አጠናክራ ልትቀጥል ሲገባትና ስትችል፡ ያን ማድረጓን ትታ፥ በቀደመው ምልጃዋ፡ "ልጄ ሆይ! መለኮታዊ ማንነትህን፡ ለዓለሙ ልትገልጥበት የወሰንኸው ጊዜህ ባይደርስም እንኳ፡ እባክህ፡ ለእኔ ስትል፡ ፈቃዴን ፈጽምልኝ!" እንዳለችው በሚያስገነዝብ ኹኔታ፡ ከልጇ ዘወር ብላ፡ በዚያ ፋንታ፡ አገልጋዮቹን ጠርታ፡ "ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!" አለቻቸው።

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ይህን፡ ራሷ፡ በቀጥታ፡ የሰጠቻቸውን ትእዛዝ፡ ወዲያው የፈጸሙት፡ እነርሱ፡ አገልጋዮቹ ብቻ አይደሉም፤ አምላክ የኾነው ልጇም፡ ያለአንዳች ተከታይ፥ ወይም፡ ተጨማሪ ጥያቄ፡ በፍጹም ታዛዥነት፡ ለፍጻሜ አበቃው እንጂ።

በዚህ፡ በእናቲቱ ትእዛዝ መሠረት፡ አገልጋዮቹ፡ ወደእርሱ፡ ወደልጇ ወደወዳጇ ቀርበው፡ "እናትህ፡ 'ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' ብላ፡ ወደአንተ ላከችን፤ ምን እንድናደርግ ትወድዳለህ? እዘዘን!" ብለው፡ በፊቱ በቆሙ ጊዜ፡ ወደእናቱ ኼዶ፡ "ምነው እናቴ? ያልኩሽን አልተረዳሺልኝምን? ምነው፡ እንዲህ አጋለጥሽኝ? 'አይኾንም!' ብዬሽ አልነበረምን?" አላለም።

የልቧን አሳብና ፍላጎት ስላወቀው፡ ከእርሷ፡ ተጨማሪ ምላሽን፡ ወይም ማብራሪያን ሳይጠይቅ፡ የእናቱን ትእዛዝ፡ ያለአንዳች ማመንታት ፈጸመ።

፫ኛ፡ የሰውን ዘርና ዓለሙን ኹሉ ሊያድን፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ የግብዣውን ጥሪ ተቀብሎ፥ ራሱም ተገኝቶ እየተጋበዘበት ባለው፡ በዘመዶቹ ሠርግ ላይ፡ ይህን የመሰለ ችግር መድረሱን ሲያውቅ፡ ቀድሞውንስ ቢኾን፡ እንዴት ዝም አለ? ከዚህም በላይ፡ እናቱ፡ ለእርሱ የሚቻለው መኾኑን እያወቀች፡ ለተቸገሩት ዘመዶቻቸው፡ ያን፡ እጅግ አስፈላጊና አስቸኳይ የኾነ እርዳታ እንዲያደርግላቸው ስትጠይቀው፡ ያን የመሰለ፡ ርኅራኄና ኀዘኔታ የጎደለው ያስመሰለውን፡ ከባድ የአሉታ ምላሽስ እንዴት ሊሰጣት ወድዶ መረጠ? ይህ የጌታ ኹኔታ፡ ለማያምን ቀርቶ፡ ለሚያምን ደካማም ቢኾን፡ ግራ የሚያጋባ ነገር ኾኖ ይታያል።

ነገር ግን፡ ለምን፡ እንዲህ ያለው ነገር እንዲደርስ ፈቃዱ እንደኾነ ለመረዳት፡ ቀደም ብሎ ወደተጠቀሰው፡ ወደመለኮታዊው ዕቅድ ዓላማ መለስ ብሎ ማስተዋልን ይጠይቃል። ዕቅዱና ዓላማው እኮ፡ የእናቱን፡ ማንነትና ክብር ለመግለጥ ስለኾነ፡ መድረኩን፡ ለእርሱ ማንነትና ክብር መገለጫ ሳይኾን፡ በሙሉ፡ ለእርሷ ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን መልቀቁን፡ በማስተዋል መመልከት ነው።

<u>የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርዋ፡ አማላጅነቷ </u>ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር እም እንደመኾኗም፥ በራሷ መለኮታዊ ፈቃድ፥ ኹሉን ማድረግ የማይሳናት መኾኑ ጭምር<u> ነው እንጂ።</u>

ይኸውም፡ “የእናት ምልጃ፡ ፊት አያስመልስ! አንገት አያስቀልስ!” እንደሚባለው፡ ይህን የመሰለው መለኮታዊ ቸርነት፡ ይደረግላቸው ዘንድ፡ ሰዎች፡ በፍጹም ሃይማኖት ኾነው፡ በስሟ፡ ወደእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋናና ጸሎት፡ በቋሚ ምልጃዋ፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን ማስገኘቱ ነው፡፡

የሰው ልጆች፡ ራሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ካበቁ፡ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ጣልቃ ገብተው፡ የመለኮትን ምሕረት ለማስገኘት የሚችሉበትን የአማላጅነት ሥልጣን ሊሰጣቸው፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ እንደኾነ፡ በዚህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቅድስት እናቱ፡ በድንግል ማርያም አሳሳቢነት በፈጸመው፡ በአዲሱ ኪዳን መለኮታዊ ተአምራቱ አረጋግጦ አሳይቷል፡፡ ያሳየውም፡ ይህ የመለኮት ቸርነት፡ እየራሳቸውን፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ ለዚህ ጸጋ ላበቁ ለሰው ልጆች ኹሉ ጭምር መኾኑን ነው፡፡

እንግዴህ፡ እግዚአብሔር እም ለተዋሓደቻት፡ ለሰብአዊቷ እናቱ ድንግል ማርያም፡ መለኮታዊ ልጇ የሰጣት ክብርና ያሳወቀላት ሥልጣኗ ይህ ነው፡፡ ታዲያ! ፈጣሪ፡ በሰብአዊ አእምሮ ሊታሰብ፥ በሰብአዊ አንደበትም፡ ሊነገር፥ በሰብአዊ ዓቅምም ሊገለጽ በማይቻል ቸርነቱና ጥበቡ ያደረገውን ይህን፡ የፍጹም ለጋሥነቱን ሥራ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ራሱ ሰው፡ በእርሷ ምክንያት ያገኘውን፡ የመጨረሻውን ታላቅ ሥልጣንና ክብር እያደነቁ በማመስገን ፈንታ፡ ሥጋውያን ሰዎች፡ “ድንግል ማርያም አታማልድም!” እያሉ፡ በዚህ ዓለም፡ በምድር፡ እርስ በርሳቸውና በመካከላቸው የሚያካኺዱትን፡ የክፉ ቅንዓትና ምቀኝነት ግንዛቤ፡ ሳያፍሩና ሳይፈሩ፡ በመለኮት ልጇና በመለኮታዊት እናት ላይ ጭምር ሊያሳዩና ሊፈጽሙ ይገባልን? የለም፥ አይገባም፡፡

## የቃና ዘገሊላ እና የቅዱስ ሚካኤል በዓላት።

ከዚህ አስከትለን፡ የ“ቃና ዘገሊላ” እና የቅዱስ ሚካኤል በዓላት፡ በጥር ፲፪ ቀን፡ አብረው እንዲከበሩ የተደረጉባቸውን ምክንያቶች፡ እናቀርባለን፡-

፩ኛ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከጥምቀቱ በኋላ፡ የእርሱና የእናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም አምላክነት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በይፋ የተገለጠው፡ በቃና ዘገሊላ ስለነበረ፡ ከጥምቀት በዓል ጋር ተያይዞና ቀጥሎ ሊከበር የሚገባና የሚያስፈልግ ኾኗል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኙበት፡ ቅዱስ ሚካኤልም፡ በዚያ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ እንዳልተለየ ስለሚታመን፡ የቃና ዘገሊላ በዓል፡ ከዚሁ ሊቀ መላእክት በዓል ጋር አብሮ እንዲከበር ማድረጉ፡ በእርግጥ፡ ተስማሚ፥ ተገቢና አመቺ ይኾናል፡፡

፪ኛ፡ በጥር ፲፪ ቀን የሚከበረው፡ የቅዱስ ሚካኤል በዓል፡ የይስሓቅና የርብቃ ልጅ የኾነው ያዕቆብ፡ የመንትያ ታላቁን፡ የዔሳውን ብኵርናና፡ ከቡራኬው ጋር፡ ከአባታቸው ከይስሓቅ በማታለል ስለወሰደበት፡ ወንድሙ፡ ሊበቀለው መፈለጉን ተረድቶ፡ ወደእናቱ ወንድም፡ ወደአጎቱ፡ ወደላባ አገር ኰብልሎ በኼደ ጊዜ፡ እዚያ፡ በኖረበት ዘመን፥ ኋላም፡ ከሚስቶቹና ከልጆቹ፥ ከብዙ ከብትም ጋር ወደወላጆቹ አገር ተመልሶ፡ ከወላጆቹ ቦታ እስከደረሰበት ቀን ድረስ፡ ከእግዚአብሔር ታዝዞ፡ ሳይለየው የጠበቀውን ቅዱስ ሚካኤልን እናዘክርበታለን፡፡

፫ኛ፡ የእሥራኤል ልጆች፡ በዘመነ ኦሪት፡ ለአርባ ዓመታት፡ በምድረ በዳ በተፈተኑበት ጊዜ፡ የብሉይ ኪዳኗ ታቦተ ጽዮን፡ በመካከላቸው ሣለች፡ ዓቃቤ መልአክ ኾኖ፡ እርሷን ያገለግልና ሕዝቡን ይጠብቅ የነበረው፡ ይኸው ሊቀ መላእክት እንደነበረ ኹሉ፡ ዛሬም፡ ለጥምቀት በዓል፡ ከቤተ መቅደሱ፡ ወደባሕረ ጥምቀቱ ወርዶ፥ በዚያም ኹለት ሌሊት አድሮ፡ እንደሌሎቹ ታቦታት፡ በጥር ፲፩ ቀን ሳይኾን፡ ወርኀዊ በዓሉ በሚውልበት፡ በጥር ፲፪ ቀን፡ ወደመንበረ መቅደሱ ከሚመለሰው፡ ከአዲስ ኪዳኑ ታቦት ሳይለይ የሚያገለግለውን፡ የዚህኑ፡ የቅዱስ ሚካኤልን ተልእኮ እናስታውስበታለን።

እነዚህ ኹሉ ሥርዓቶች፡ አማናውያን፡ ማለትም፡ እውን የሚኾኑት፡ አምልኳችን፡ እንደእግዚአብሔር ቃል፡ “በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ” መፈጸሙን በየራሳችን ስናረጋገጥ ብቻ መኾኑ፡ ምንጊዜም መዘንጋት የለበትም።

## የቅዱሳን አማላጅነት ተረጋግጦ የተመሰከረበት ኹኔታና ከእኛ የሚጠበቀው ሃይማኖታዊ ምግባር፡፡

እግዚአብሔር፡ ስለቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ፡ በገሃድ ያሳየውን የመሰለ፡ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊቱን፡ በብሉዩ ኪዳንና በአዲሱ ኪዳን ዘመናትም መፈጸሙ ታይቷል፤ ከእነዚህም መካከል፡ አንዳንዶቹን፡ እንደሚከተለው፡ በምሳሌነት መጥቀሱ፡ አግባብና የሚበቃ ይኾናል፡-

፩ኛ. የብሉዩን ኪዳን በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ ኖሮ÷ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና በእርሷ ብቻ ተወስኖ፡ ከእርሷ ልጆችን ከወለደ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ፡ ወደግብፅ ልኮት፡ የእሥራኤልን ልጆች፡ ከባርነት ነጻ ባወጣቸው፡ በሙሴ ላይ ስለደረሰው ገድል የሚያስታውሰው ዜና መዋዕል ይገኛል፡፡

አዎን! "የእሥራኤል ልጆች" ይባሉ የነበሩት አይሁድ፡ የቀይ ባሕርን፡ በአምላካቸው ተአምራዊ ኃይል ከተሻገሩ በኋላ፡ ሙሴ፡ ስለሚቀጥለው አካኼዳቸው፡ መለኮታዊዉን መመሪያ፡ ከፈጣሪው ለመቀበል፡ ወደደብረ ሲና ወጥቶ፡ በሱባኤ፡ ለአርባ ቀናት ቢዘገይባቸው፡ ወንድሙን፡ አሮንን፡ "እንደአሕዛብ፡ በፊታችን የሚኼድ ጣዖትን ካልሠራህልን!" ብለው አስጨንቀው፡ ላቆሙት የጥጃ ምስል መስገዳቸውና መሠዋታቸው ይታወሳል።

እግዚአብሔርም፡ ይህን ግብራቸውን አውቆ፡ **"ይህ ሕዝብ፡ አንገተ ደንዳና ነው፤ አኹንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸውና እንዳጠፋቸው ተወኝ! አንተንም፡ ለታላቅ ሕዝብ መሪ አደርግሃለሁ!"** ባለው ጊዜ፡ ሙሴ፡ ስለሕዝቡ፡ በአምላኩ ፊት ጸልዮ እንዳማለደ÷ **"እግዚአብሔርም፡ በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፉ ነገር ራራ፡፡"** በሚለው፡ የአሪቱ ቃል መሠረት፡ ለሕዝቡ ምሕረትን እንዳስገኘ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ተረጋግጧል፡፡ (ዘጸአ. ፴፪÷ ፯-፲፬፡፡)

፪ኛ. የአዲሱን ኪዳን በሚመለከት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተናገራቸው ቃላት፡ እግዚአብሔር፡ ለበቁት የሰው ልጆች፡ በሕይወተ ሥጋም ሣሉ÷ በሕይወተ ነፍስም እያሉ ለሰጣቸው የማማለድ ጸጋ በቂ ማስረጃዎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል፡ እንዲህ የሚሉትን፡ ለአብነት ያህል፡ እንጠቅሳቸዋለን፡-

"እናንተን የሚቀበል፡ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል፡ የላከኝን ይቀበላል:: ነቢይን፡ በነቢይ ስም የሚቀበል፡ የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፤ ጻድቅንም፡ በጻድቅ ስም የሚቀበል፡ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል:: ማንም፡ ከእነዚህ ከታናናሾቹ፡ ለአንዱ፡ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃን ብቻ፡ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ዋጋው አይጠፋበትም::" (ማቴ. ፲፥ ፵-፵፪።) "እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" (ዮሐ. ፲፬፥ ፲፪።)

እዚህ ላይ ግን፡ በብርቱ ልናስተውለውና ልንፈጽመው የሚገባን፡ አንድ ታላቅ፡ ሃይማኖታዊ ቊም ነገር አለ፤ ያም ቊም ነገር፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ብቻ ሳይኾን፡ "ያማልዱናል!" ብለን፡ ዘወትር የምንማፀናቸው፡ የነቢያትና የሓዋርያት፥ የጻድቃንና የሰማዕታት፥ የቅዱሳን መላእክት ጭምር፡ የፈቃዳቸውና የፍላጎታቸው፥ በተለይ፡ በቅድሚያ የተገለጹት ቅዱሳንና ቅዱሳት፡ የገድላቸውና የመሥዋዕትነታቸው፡ ዋና ዓላማና ግብ፡ እኛ ወገኖቻቸው፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ እያንዳንዳችን፡ እነርሱ ለደረሱበትና ለተቀዳጁት ጸጋና ክብር፡ እየራሳችንን አብቅተን እንድንገኝላቸው እንጂ፡ በእነርሱ ምልጃ ብቻ ተማምነን፡ የዚህ ዓለም፡ ሥጋዊ ኑሮአችን፡ በሞት እስኪያበቃ እንድንቆይ አለመኾኑ ነው::

## አስተርእዮ ማርያም:- የድንግል ማርያም፡ ፍልሰተ ሥጋ ዜና::

## "አስተርእዮ" ምን ማለት ነው? መልእክቱስ፡ ምንድር ነው"

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ መታሰቢያ በዓል፡ በየዓመቱ የሚውለው፡ ጥር ፳፩ ቀን ነው። እርሱም፡ "አስተርእዮ ማርያም" በሚል ስያሜ ይጠራል፤ በዓሉ፡ እንዲህ ባለ ስያሜ ሊጠራ ያስፈለገበትን ምክንያት ለማብራራት፡ ይኸው ምክንያት፡ ታላላቅ የኾኑ አምላካውያት ምሥጢራት የተከሠቱበትን ኹኔታዎች ያካተተ በመኾኑ፡ ሰፊና ጥልቅ ቢኾንም፡ በጥቂቱ ሳንገልጸው አናልፍም።

በመጀመሪያ ነገር፡ "አስተርአየ" የሚለው፡ የግእዙ ቃል፡ "አሳየ፤ ገለጠ፤ አበራ፤ ነገረ፤ አስተማረ፤ አሳወቀ፤ አስረዳ" ማለት ነው። "አስተርእዮ" የሚለውም ቃል፡ ከዚሁ የተገኘ ሲኾን፡ "የገለጠበት፥ የተገለጠበት፤ ያሳየበት፥ የታየበት፤" ማለት ነው። ምኑን የገለጠበትና ያሳየበት? ማንነቱንና ምንነቱን ነዋ! ምን ኾኖ፥ እንዴትስ ኾኖ የተገለጠበትና የታየበት? ይህ ኾኖ፥ እንዲህም ኾኖ የተገለጠውና የታየው፡ እርሱ፡ ማነው? "እውነትና መንፈስ የኾነው፡ እርሱ፡ የማይታየው፡ ፈጣሪና የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፡ በገሃድ ሊገለጥና በግዘፍ ሊታይ፡ ሰው ኾነ! በሰውነት ተገልጦ ታየ!" ለማለት፡ ይህ ኹሉ መለኮታዊ ትንግርት የተፈጸመበት ወራት፡ "አስተርእዮ" ተባለ።

ይህ አስተርእዮት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት የመገለጡና የመታየቱ ምሥጢራዊ ትንግርት የተፈጸመበትን ኹኔታ፡ እስኪ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል እናቅርበው!

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት አካሏና ባሕርይዋ፡ በተፈጠረችበት በእግዚአብሔራዊው መልኳ፥ በእርሱ በፈጣሪዋም፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነች!" በተባለችበት አምላካዊ ማንነቷ፡ ራሷን፡ ለዚያ ፍጹምነት አብቅታ ተገኘች። በዚህ ጊዜና ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡-

በቅድሚያ፡ ለሌላ ለማንም ፍጡር ተገልጦና ታይቶ ሊታወቅ ባልቻለ የአስተርእዮቱ ምሥጢር፡ ከፈጣሪ በኩል፡ ራሱ እግዚአብሔር፥ ከቅዱሳን መላእክቱ ወገን፥ ቅዱስ ገብርኤል፥ ከሰብአውያን ፍጡሮቹም በኩል፡ ራሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እኒህ ሦስቱ ብቻ ባወቁት ክሥተትና ርእዮት፡ የድኅነቱ ምሥራች በተነገረበት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን፡ ፭ሺ፬፻፺፱ ዓመተ ኪዳን፡ እግዚአብሔር እም በተዋሓደቻት፡ በእርሷው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ በትስብእትነት ተፀነሰ፤

ቀጥሎ፡ የአስተርእዮቱን አድማስ፡ በበለጠ በማስፋት፡ በፈጣሪ በኩል፡ ራሳቸው ቅድስት ሥላሴና በመንበረ ጸባዖቱ ዙርያ ያሉትን፥ በሱራፌልና በኪሩቤልም የታቀፉትን አርባዕቱ እንስሳን፥ ከቅዱሳን አንጋደ መላእክትም፡ ከነመንጎቻቸው፡ በሜዳ ሠፍረው በነበሩ እረኞች ዘንድ የታዩት፡ የሰማይ መላእክት፥ የምድር ሠራዊት ከኾኑት፡ ከሰው ወገኖች ደግሞ፡ እነቅዱስ ዮሴፍና ሕፃኑን ኢየሱስን ያሟሙቁት እንስሳት፥ እረኞቹም፡ ከነመንጎቻቸው፥ ከዚያም፡ እነሰብአ ሰገል ብቻ ባወቁት፡ የምሕረቱ ዓመት በባተበት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በሰውነት ተወለደ፤

እንዲህ፡ በፍጹም ሰውነት፡ እስካኹን፡ ለጥቂቶችና ለብዙዎች ብቻ የተገለጠውና የታየው እግዚአብሔር፡ አኹን ደግሞ፡ ይኸው፡ እውነተኛ ማንነቱና ምንነቱ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ በሙሉ፥ ለኹሉም፡ በይፋ ይታወቅ ዘንድ፡ በጥር፡ ፲፩ ቀን፥ ፴ ዓመተ ምሕረት፡ ሰማዩ ተከፍቶና አባቱ እግዚአብሔር አብ፡ "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘአፈቅር፡ ዘቦቱ ሠመርኩ!"

ማለትም፡ "ቀድሞ፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በሰውነት፡ ከእግዚአብሔር እም ቅድስት ድንግል ማርያም የወለድሁት፡ የምወድደው፥ በእርሱም ደስ የምሰኝበት ልጄ፡ ይህ ነው!" ብሎ ቃሉን በማሰማት፣

እናቱ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በወንዙ አጠገብ ቆማ፡ የራሷንና የእርሱን ማንነትና ምንነት፡ በእናትነቷ በማረጋገጥ፣

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ "ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ፤ ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር፡ እንዘ ይወርድ፡ በአምሳለ ርግብ፤ ወነበረ ላዕሌሁ።"

ማለትም፡ "እነሆ! ሰማይ ተከፈተለት፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ፡ በርግብ አምሳል፡ ሲወርድ፥ በእርሱም ላይ ሲያርፍበት አየ።" እንደተባለ፡ ከሰማይ ወጥቶ በሚበርር ርግብ ተመስሎ ወርዶ፡ በላዩ በማረፍ፥

ራሱ አጥማቂው ዮሐንስም፡ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፣ ዘየአትት፥ ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም!"

ማለትም፡ "እነሆ፡ የዓለሙን ኃጢአት ኹሉ፡ ፈጽሞ የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ!" ካለ በኋላ፡

"ወበውእቱ፡ ያጠምቀክሙ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት!"

ማለትም፡ "በመንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም የሚያጠምቃችሁ፡ እርሱ ነው!!" ብሎ፡ ለደቀ መዛሙርቱ በማመልከት፡ ኹሉም፡ ስለማንነቱ መስክረውለት፥በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። (ማቴ. ፫፥ ፲፩-፲፯። ዮሐ. ፩፥ ፳፱ እና ፴፯።)

በዚህ መልክና ይዘት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን በኾነው ፅንሰቱ የተጀመረውና በመስከረም ፩ ቀን በኾነው ልደቱ የቀጠለው፥ ሲካኼድ ቆይቶም፡ በጥር ፲፩ ቀን በኾነው ጥምቀቱ ያበቃው፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት በመገለጥና በመታየት የፈጸመው የቸርነት ሥራው፡ እየታሰበ የሚከበርበት፡ በተለይ፡ ከጥር ፲፩ እስከ ሦስቷ ቀን "በዓለ ኢትዮጵያ" (ጾመ ኢትዮጵያ = ጾመ ነነዌ) መግቢያ ድረስ ያለው ወራት፡ "አስተርእዮ" ተባለ።

## የድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ ዜና።

## "ፍልሰታ" ምንድር ነው?

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት፥ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ፡ ብዛታቸው፡ ሊቆጠር የማይቻል፡ መልካካም ነገሮችን፡ ላበረከተልን ፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር፡ እንደምናደርገው ዅሉ፥ "እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን" ስለዀነችው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በየኅሊናችን የምናስበው፥ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሕዋሳታችን የምንፈጽመውም ዅሉ፡ በየሕይወታችን ውስጥ፡ ዐብሮን ሕያው ዅኖ፡ ለዘወትር፡ ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ፡ በአንድ ቀን፥ ወይም፡ በአንድ ሳምንት፥ ወይም፡ በአንድ ወር፥ ወይም፡ በአንድ ዓመት ብቻ፡ የተወሰነ አይደለም።

አዅንም እዚህ ላይ አቅርበን የምንጽፍላችሁ፡ የእመቤታችን ዜና መዋዕሏ፡ በተለይ፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሐፍ ውስጥ፡ ተመዝግቦ የሚነበበውን፥ ልጇ ወዳጇ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ [ክርስቶስ]፡ እስካረገበትና መንፈስ ቅዱስ፡ በሐዋርያት ላይ፡ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውን ሳይዀን፡ ከዚያ በኋላ፡ በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው፡ ምድራዊ ሕይወቷ፡ በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ ካበቃበት፡ ከ"ፍልሰቷ"፡ ማለትም፡ ሕያው በዀነው በአካለ ሥጋዋ፡ ከምድር፡ ወደገነት ተነጥቃ ከተወሰደችበት፡ ከዚችው ከጥር ፳፩ ቀን ተነሥተን፡ የመጨረሻ የዀነውን፡ ዜናዋን ብቻ ያካተተውን ዝክረ ነገር የምናስታውስበት ይዀናል፤ እርሱም፡ ይህንኑ፡ የመጀመሪያውን የፍልሰቷን በዓል በምናከብርባት፡ በዚችው፡ በጥር ፳፩ ቀን፡ እንዲህ በሚለው ቃል ይገለጻል፡-

የእመቤታችን ፍልሰት የዀነው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ በዕለተ እሑድ ነው። "ፍልሰት"፥ ወይም፡ "ፍልሰታ" የሚባሉት አርእስት ቃላት፡ "ፈለሰ" ('ለ' ሳይጠብቅ) ከሚለው፡ "ከቦታ ወደቦታ መዘዋወርን"፡ ማለትም፡ "አንድ ሰው፡ ካለበት ቦታ ተነሥቶ፥ ወይም፡ መኖሪያውን ነቅሎ፡ ወደሌላ ተወሰደ!" የሚል ትርጕምን ከሚያመለክተው፡ ከግእዝ ዘር የተገኘ ዘይቤ ነው፤ በኢትዮጵያኛ፡ "ለ" ጠብቆ፡ "ፈለሰ" ያሰኛል።

ከዚህ የተነሣ፡ የእመቤታችን ሕያው ሰውነት፡ ከምድር፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የመወሰዱን ተአምር ለማስረዳት፡"ፍልሰታ" እንላለን።

ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ መቼ ይመስላችኋል? መነገር የጀመረውማ፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተፈጽሞበት፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሶ የወለደውንና ዐጥብቶ ያሳደገውን፡ ያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ አይሁድ፡ እጅግ በከፋው አላዋቂነታቸውና ሰይጣናዊ አስተሳሰባቸው፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ ነው።

ለእነርሱ መዳን ሲል፡ ለመሥዋዕትነትና ለቤዛነት፡ በሰውነት መጥቶ፡ ያን ተልእኮውን ፈጽሞ፡ ወደክብሩ በተመለሰው፡ በልጇ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ ሰውነት ላይ፡ አድርገውት የነበረውን፡ ያንኑ ግፍና ጭካኔያቸውን፡ አኹንም፡ በዚያ፡ በእርሷ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ መለኮታዊ ሰውነት ላይ ለመፈጸም ባሰቡበት፥ በማሰብም ብቻ ሳይወሰኑ፡ አዎን! በሞከሩበት ጊዜ እንጂ።

እርሷንማ፡ እንኳን ሞት፡ የጨረፍታ ያህል እንኳ፡ አንዳች ጉዳት ሊያልፍባት እንደማይቻል፡ አኹንም፡ ገና አላወቁም። ገና ከመጀመሪያው፡ በፍጹም ሃይማኖቷና ምግባሯ፡ ሰውነቷን ለአምላክነት በማብቃቷ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻትን፥ የእግዚአብሔር አብ ሙኸሪት ኾና፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አንድዬ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በመለኮትነትም፥ በሰውነትም፡ የወለደችለትን፡ የእርሷን፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ሰውነት፡ እንዴት፡ ክፋትና ኃጢአት፥ ሞትና መቃብር፥ መበስበስና ሌላውም ዓይነት ጉዳት፡ እንኳንስ ሊደርስበት፡ ሊቀርበውም እንኳ፡ አዎን! እንዴት ይቻለዋል? ፈጽሞ አይቻለውም።

እንኳንስ እርሷ፡ በእርሷና በልጇ በማመን፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁት ኹሉ እንኳ፡ በእርሷና በልጇ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ምክንያት፡ ከክፋትና ከኃጢአት፥ ከሞትና ከመቃብር መበስበስ ሳይቀር፡ ነጻ ኾነው፡ ምንም ዓይነት ጉዳት በሌለበት፡ በዘለዓለሚቱ የሰንበት ዓለም፡ ቅድስቲቱን የትንሣኤ ሕይወት፡ እንደሚኖሩ፡ አዎን! ገና አላወቁም።

እርሷም፡ እነዚያ ክፉዎቹ አይሁድ፡ በእርሷ ሰውነት ላይ ሊያደርጉ ያሰቡትን፥ አስበውም አልቀረ፡ የቃጡትን ያን ጉዳት ሊያደርሱ እንደማይቻላቸው፡ በመለኮታዊው ኃይሏ፡ እንደሚሰማቸው አድርጋ፡ አሳወቀቻቸው።

ከዚህ በኋላ፡ በመላእክት ተነጥቃ፡ ወደገነት ተወሰደች።

ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ አዎን! ይህ መለኮታዊ ትንግርት ከተፈጸመበት፡ ከፍልሰቷ ዕለት፡ ከጥር ፳፩ ቀን አንሥቶ ነው።

"መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ"፥ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የምንላት፡ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንዲህ፡ በመላእክት ተነጥቃና ታጅባ፡ ወደገነት በፈለሰች፥ በተወሰደች ጊዜ፡ የኾነውን ደግሞ እንስማ!

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፡ ቅዱስ ሥጋውን እየቆራረሰና ክቡር ደሙንም እያፈሰሰ፡ የቤዛነቱን ተልእኮ እየፈጸመ ባለበት ሰዓት፡ ከመስቀሉና ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አጠገብ ሳይለይ፡ የዚሁ ልጇን አደራነት ተቀብሎ፡ እርሷን፡ እናት፥ ራሱንም፡ ልጇ አድርጎ፡ ይጠብቃት የነበረው፡ ይኸው ወንጌላዊው ዮሓንስ፡ አኹንም፡ ዐብሯት ኾኖ፡ ይህንኑ የፍልሰቷን ምሥጢር ለማየት የበቃ ኾነ።

ሌሎቹ ሓዋርያት ግን፡ ይህን ታላቅ ተአምር ባለማየታቸው፡ በሚቀጥለው፡ በነሓሴ ፩ ቀን፡ የኹለት ሳምንት ሱባዔን ጀመሩ።

ይኼም ሱባዔያቸው፡ የነገሩን ኹሉ፡ እውነተኛ ምሥጢር ስለገለጠላቸው፡ ፍሬያማውን ምላሽ ማግኘት እንደቻሉ አረጋገጡ።

የዚህንና የተከታታዮቹን ኹለት ሱባኤዎች፡ ዝክረ ነገር፡ በሚቀጥለው የነሓሴ ወር በሚከበረው፡ በእግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰተ ትንሣኤዋ በዓል ዕለት እናቀርበዋለን።

## ኪዳነ ምሕረት።

እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ከእግዚአብሔር እም ቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘው፡ የመጨረሻው፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ "ኪዳነ ምሕረት" ይባላል። የዓመቱም በዓል፡ የካቲት ፲፮ ቀን ይውላል።

የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ የፈጣሪያቸውን ፈቃድ መተላለፋቸው፡ በየራሳቸውና የእነርሱን ፈለግ በተከተሉ ልጆቻቸው ላይ፡ የዲያብሎስን ገዢነት፥ የኃጢአትን ቀንበርና የሞትን ፍዳ አመጣባቸው።

በየዘመናቱ፡ ለደጋጎች ልጆቻቸው የተሰጡት፡ አምላካውያት ቃል ኪዳናትና የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ንስሓቸው ግን፡ አስቀድሞ፡ እግዚአብሔር እምን፥ ቀጥሎም፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ከሰማየ ሰማያት ልዕልናቸው፡ ወደምድር አውርዶ፡ ሰው እስከመኾን አደረሳቸው፤ መለኮታዊውም ፈቃድ፡ የመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን በኾኑት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ስለተፈጸመ፡ ይህ፡ ፍቅርና ርኅራኄ፡ የሰው ልጆች፡ የእግዚአብሔር ልጆች የኾኑበትን፡ የመጨረሻውን ክብር አቀዳጃቸው፤ የኃጢአትን ሥርየትና የትንሣኤን ሕይወትም አስገኘላቸው።

ይህ፡ የልጅነት ጸጋ፥ ይህ፡ የሥርየት ነጻነት፥ ይህ፡ የትንሣኤ ክብር፡ ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖር ዘንድ፡ በመለኮታዊ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ታተመ!

ማኅተሙም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ የተዋሐደውና በመስቀል ላይ የሠዋው፥ ዛሬም፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በንስሓ ነጽተን፡ ከቅዳሴ ጸሎት በኋላ የምንቀበለው፡ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው።

በእርሷ፡ በእናቱ፡ በድንግል ማርያም፥ በእርሱ፡ በልጇም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነትና ሰውነት የተዋሕዶ ምሥጢር፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፥ በተለይም፡ ለሰው ዘር፡ የተገኘው፡ ይህ ኹሉ ጸጋና በረከት፡ "ኪዳነ ምሕረት" ተብሎ፡ በያመቱ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦ ይከበራል።

\+ \+ \+